# ከተማና መሰረተልማት ሚኒስቴር

# አዲሱ የከተማ ልማት ረቂቅ ፖሊሲ

*የፖሊሲና ስትራቴጂ ጥናትና ምርምር ስራ አስፈጻሚ*

*ጥቅምት፣ 2016 ዓ.ም*

# የአቀራረብ ይዘት

1 መግቢያ

1.2 የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች

**2. የነባሩ ፖሊሲ ግምገማ**

**2.1 ጥቅል የፖሊሲ ማሻሻል ገፊ ሁኔታዎቸሀ**

**2.2 ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ  ስምምነቶች**

**3 የፖሊሲው ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማዎች፣ግብና መርሆዎች**

**4 አጠቃላይ የፖሊሲው ግብና ዋና ዋና ዓላማዎች**

**5. የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮች፣ግቦችና አቅጣጫዎች**

**6 ማስፈጸሚያ ስልት**

**7 ውጤት አመላካቾች**

# አንድ፡ መግቢያ

- ከተሞች የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ሁነቶች ተግባራዊ የሚሆኑባቸው ማዕከላት ሲሆን ከገጠር ማዕከል የሚለይበት ይዘት የኢኮኖሚያዊ ሁነቱ በማኑፋክቸሪን ኢነዱስተሪ፣ ሰረቪስ፣ ንግድ፣ ቱሪዚምና ትራንስፖርት የሚገለጽ፤ ማህበራዊ ዘይቤው ከተሜነት ስለሆነ ነው፡፡
- የሰው ልጅ ከተሞችን እንደ ዋና የመኖሪያና ሥነ-ሕዝባዊ ክምችት ማዕከልነት የመጠቀም ፍላጎቱ በከፍተኛ ሁኔታ አድጓል፡፡

# መግቢያ…

- በአሁኑ ወቅት ከዓለማችን ግማሽ በላይ ሕዝብ በከተሞች ይኖራል፡፡ በቀጣይ 2050 ይህ አሀዝ ወደ 70 % ያድጋል (የዩኤን፣ 2022 ጥናት)
- **ስለዚህ የፕላኔታችን ቀጣይ እጣ ፈንታ መከተም ይሆናል**
- የኢትዮጵያ የከተማነት ምጣኔ ዝቅተኛ ነው በ2015 ዓ.ም 22 በመቶ አካባቢ (አ/ባንክ) 25 (CSA)ይ አሀዝ በታዳጊ ሀገራት ደረጃ ዝቅተኛ ሊባል የሚችል ነው ነገር ግን የክትመት መጠነ እደገቱ እጅግ ፈጣን ነው (5.4%) በማደግ ላይ ይገኛል በአለም ደረጃ ከፍተኛ ፍጥነት ነው
- ለዚህም ገፊ ምክንያቶች ተብለው የሚጠቀሱት ከገጠር ወደ ከተሞች የሚደረግ ፍልሰት፤የከተማ ነዋሪው ተፈጥሯዊ የወሊድ ምጣኔ ኩነት እና የአዳዲስ ከተሞች ምስረታ ናቸው፡፡

- የኢትዮጵያ የከተሞች ግምገማ (Ethiopian urbanization review, 2015) እንደሚያሳየው የከተሞች መስፋፋት በሚቀጥሉት  ግዜያት የበለጠ ፈጣን (5.4% rate of urbanization per annum)፡፡
- **ይህ ማለት እ.ኤ.አ. ከ2028-2034 የከተማ ነዋሪ ህዝብ በሦስት እጥፍ ይጨምራል ስለሆነም  በቀጣይ 10 አመት ውስጥ 30% የሚሆነው የአገሪቱ ህዝብ በከተማ ይኖራል።**
-  ከፈጣን የከተሞች መስፋፋት ጋር በትይዩ ኢትዮጵያ በሥነ ሕዝብ አወቃቀር በፍጥነት የለውጥ ሂደት ውስጥ ትገኛለች።
- **የሠራተኛ ኃይሉ ከባለፉት 20 ዓመታት በእጥፍ አድጓል ለቀጣይ እ.ኤ.አ በ2030 በ2005 ከነበረበት 33 ሚሊዮን  ወደ 82 ሚሊዮን እንደሚያድግ ትንበያው ያሳያል፡፡**

# ቀጠለ…

- የከተሞች መስፋፋት ከፍተኛ ሀብትና ዕድሎችን የሚፈጥር፣ ሀብትን በተሻለ ሁኔታ ለመጠቀምና አዳዲስ እድሎች የሚፈጥር ቢሆንም፣ በብዙ አገሮች በተለይም በማደግ ላይ ባሉ አገሮች እነዚህ ገጽታዎች ለልማት **የሚውሉ አይደሉም።**
- እንደውም በታዳጊው ዓለም የከተሞች መስፋፋት ፈተናዎች ከልማት ትርፉ የሚበልጡ ይመስላሉ።
- **ለዚህ ደግሞ ምክንያት የሚሆነው ጥናቶች እንደሚያሳዩት በንደነዚህ አይነት አገራት ከተሞች ሁሉአቀፍ ፖሊሲ ተበጅቶላቸው ስለማይመሩና ቅንጅታዊ አሰራርና አሳታፊ የፖሊሲ አሰራርና አተገባበር ስለሚያንሳቸው ነው።**

# የቀጠለ....

- ስለዚህ በከተሞች የሥራ ዕድል በመፍጠር ኢትዮጵያ የዲሞግራፊ ክፍሏን ለመጠቀም ሁሉአቀፍ የከተማ ልማት ፖሊሲ የግድ ይላል፡፡
- በ1997 ዓ.ም  የከተማ ልማት ፖሊሲ ተቀርፆ ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ሲተገበር ቆይቷል፡፡
- **የፖሊሲው ትግበራ በርካታ በጎ ውጤቶች ያስመዘገበ ቢሆንም፣ በአንጻሩ ደግሞ ያልፈታቸው ችግሮችን ለመፍታትና አዳዲስ ክስተቶችን በማካተት የፖሊሲውን ወቅታዊነት ገምግሞ አዲስ ፖሊሲ መቀየስ ተገቢ ሆኗል፡፡**

# 1.2 የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች (9)

1.

ከተሞች ከገጠሩ ክፍለ-ኢኮኖሚ ጋር ያላቸው ትስስር ደካማ መሆን።

- በአንድ በኩል ከተሞቻችን ጠንከር ባሉና እሴትን በሚጨምሩ የኢኮኖሚ አውታሮች ማቅረብ አለመቻል፤ በሌላ በኩል የገጠር ክፍለ-ኢኮኖሚ ለከተሞች በቂ ግብዓት የማያቀርቡ በመሆናቸው **ከውጪ ሀገራት ለሚገቡ ሸቀጦች ማራገፊያ ለመሆን የተመቹ ሆነዋል።**
- በሀገራችን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣትና መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ በቀጣይ የከተማ ሚና በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያድግ ይጠበቃል ይህም እውን የሚሆነው በጠንካራ ሊንኬጅ ነው።

# 1.2 የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች……

2. ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚደረገውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት ከተሞች ያላቸው የኢንዱስትሪ፣ የአገልግሎትና የገበያ ማዕከልነት ሚናቸ

- የከተሞች ለተፋጠነ ኢኮኖሚያዊ እደግት መሰረታዊ ግልጋሎቶችና የከተማ ስራ አመራር ስርዐት
- የተቀናጀ የመሰረተልማት አቅርቦትና አስተዳደር
- ተመጋጋቢ የከተማ ግብይት ትስስር
- ተገቢ የኢኮኖሚና ኢነደዱስትሪ ከከተማ ቦታ ማስተሳሰር (sepace and function )
- የትኩረት እቅድ (ስትራቴጂካዊ ዕቅድና አፈጻጸም መስተጋብር)

# 1.2 የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች……

3. የከተሞች በፕላን የመመራት አቅም ውሱንነት

- ከተሞች ከቁጥጥር ውጭ መለጠጥና በፕላን ካለመመራት የመነጨ ከፍተኛ የመሰረተልማት ተደራሽነት ችግርና በአስገዳጅ መልኩ ኢመደበኛን ወደመደበኛ ማካተት (sprowling)
- የማህል ማረጀትና መበስበስ (dilapidation)

4

# 1.2 የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች……

4. የመሰረተልማት በቂ አለመሆንና ተመጋጋቢነት ዉስንነት

- ለከተሞች በአግባቡ ማደግ ከቦታ ቦታ የሚደረግ እንቅስቃሴን /ሞቢሊቲን/ የሚያፋጥንና አካባቢዎች እንዲያድጉ የሚያደርግ፤ ዘላቂነትን የሚያረጋግጥ ፕላን ይፈልጋል፡፡
- የከተማ- ከተማ ተመጋጋቢነት ለማጎልብትና የከተማ- ገጠር ትስስርን ለማስጠበቅም ከክልላዊና ሀገራዊ ፕላን ጋር የተናበበ ማድረግ የግድ ነው፡፡
- ለከተሞች ዕድገትና ሚናቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ተደራሽ መሠረተ ልማት፤ አገልግሎት አሠጣጥ መኖር እንዲሁም በቂ ፋይናንስና ዘመናዊ አስተዳደር መዘርጋት ለከተሞቹ ማደግ አስቻይ ቅደመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

## 1.2 የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች……

5. ሰፊ የቤት እጥረት፣ የተደረሽነትና ያሉት ቤቶች ከደረጃ በታች መሆን (Slums proliferations)፣

- አሁን ያለው የአገራችን የከተሜነት የዕድገት ምጣኔ ደረጃ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ እና አሁን ካለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ያልተሟላ ፍላጎት በተጨማሪ ለሚኖረው የሕዝብ ቁጥር መጨመር ጫና መልስ መስጠት የመኖሪያ ቤትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የመሠረተ ልማትና አገልግሎቶች በዓይነትም በመጠንም ማሳደግ፣ የመሬት አስተዳደርን ማሻሻል እና ማዘመን ትልቁ የአዲሱ ከተማ ልማት ፖሊሲ የርብርብ ማዕከል ይሆናል፡፡

## 1.2 የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች……

6

መሬት በፍላጎት ልክ ማቅረብ አለመቻልና በብልሹ አሠራር ምክንያት ሕገወጥ የመሬት መቀራመት መስፋፋት፣

- በከተሞች ያለው የመሬት አስተዳደር ደካማ ከመሆኑም ባሻግር፣ የተለያዩ የግል ኢንቨስትመንቶች በመሳብ በከተሞች እየተንሰራፋ ችግር መፍታት አዳጋች መሆን
- ደካመ የመሬት መረጃ አያያዝና ካደስተር
- የመሬት አቅርቦትና ፍላጎት የተመጣጠነ አለመሆኑ
- የከተማ መሬት አቅርበት አማራጭ ሞዳሊቲዎችን አለመፍጠር
- የከተማ ኢኒቬስትመንት ዜጎችን ማፈናቀል
- የመሬት በህገወጥ መንገድ በመያዝ ስፔኩሌት ማድረግ

1.2 የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች……

7. የከተሞች እድገት ያልተመጣጠነና እርስበርስ የማይመጋገቡ መሆን፣

- የከተሞች እድገት ያልተመጣጠነ ከመሆኑም ባሻገር የከተሞች ቅደም ተከተል (Urban hierarchy) በራሱ ዳግም ፕራይማሲ ሊፈጥር የሚችል፣
- ሁለተኛ ደረጃ ከተሞች አለመፈጠራቸው ከከተማ ከተማና ከገጠር ከተማ ፍልሰተን የሚያነሳሳ
- ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የመሠረተ ልማትና አገልግሎቶች ተደራሽ ለማድረግ ፈታኝ መሆን
- ኢመደበኛ እነቅስቃሴ

8. **የግል ዘረፉን ሚና የሚያጎላ በቀጣይነት የሚመራና የሚደግፍ አመለካከትና አሰራር አለመኖር፤**

- በከተሞች የሚስተዋሉትን ዘረፈ ብዙ ችግሮችን የግሉን ዘርፍ በማሳተፍ ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት ለአብነት፡
- የቤት አቅረቦት፣ የመሰረተልማት አቅርቦትና ጥገና፣ የከተማ ቱሪዚምና ኢንቬስትመንት ለገረሉ ሴክተር በቂ ኢድል በመሰጥጥ መንግስት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር ችግሮችን የመፍታት የፖሊሲ ማዕረቀፍ ውሱንነት

## 1.2 የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች……

9 ዘላቂና ለአይር ንብረት የማይበገር የከተማ ልማት መርህ ውስን መሆን (sustainability and resilience)

- በሀገራችን እየታየ ካለው የከተሞች መስፋፋትና የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ተያይዞ የከተሞች የጽዳት፣ የአረንጓዴ መሰረተ ልማትና ዉበት ውሱንነትና በቂ ስትራቴጅ ነድፎ የሚመራበት ማእቀፍ

# ክፍል ሁለት፡ የነባሩ ፖሊሲ ግምገማ


## ጥንካሬ

- ከነባሩ የከተማ ልማት ፖሊሲ በፊት ከተማ ሲመራ የነበረውን እውነታ በመቀየር፣
- ለዘርፉ ግልጽ አቅጣጫ ማስቀመጡ፤ ከተሞች እውቅና አግኝተው እንዲደራጁ ማስቻሉ፤
- የፖሊሲው ዋና የትኩረት መስኮች ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ማስፋፋት፣
- የከተማ መሬት አቅርቦትና አጠቃቀም፣ በፕላን እንዲመራ ማድረግ፣
- የቁጠባ ቤት ማስፋፋትን ማእከል ያደረገ የቤት ልማት ማፋጠንና ከባለሀብቱ ጋር በአጋርነት መሥራት፣
- ፖሊሲ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች
- የተቀናጀ የቤት ልማት

## ውስንነት


- በይዘት ደረጃ ለከተማ ወሳኝ ሚና ያላቸው ፖሊሲው ያላካተታቸውና የቅኝት ለውጥ የሚስፈልጋቸው ጉዳዮች ነበሩ፡፡
- በተለይም በከተማ ሥራ አመራር፣ በከተሞች የልማት ፋይናንስ፣ በከተማ ኢኮኖሚ፣በከተማ ግብርና፣
- በከተማ ምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት
- በዘላቂ የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ፣በከተማ ፅዳትና አረንጓዴ ልማት፣ በከተሞች ሠላምና ደህንነት፣
- በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እና በአካታች የከተማ ልማት ሥርዓት በነባሩ ፖሊሲ የተስተዋሉ ክፍተቶች ነበሩ፡፡
- ከተሞች በፕላን ኢነዲመሩ ማስቻል ክፍተት

# 2.1 ጥቅል የፖሊሲ ማሻሻል ገፊ ሁኔታዎቸሀ




- ወጫዊ አለም አቀፋዊ ሁኔታዎች
- ሀገራዊ ለውጥ
- የተለዩ የሴክተሩ ፍላጎቶች
- ነባሩ ፖሊሲ ያልዳሰሳቸው ግን በአፈጻጸም የተለዩ

# 2.2 ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶች



**SDGs**

**Africa Agenda 2063**




**Paris climatic agreement**

**New UN Urban Agenda**




# 2.3 ሀገራዊ ለውጥ- policy alignment with prosperity




ኢኮኖሚክ ሪፎርም
ECONOMIC REFORM



# 4. የፖሊሲው ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማዎች፣ግብና መርሆዎች

## ርዕይ

*"ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ሽግግር ስኬት በአግባቡ የሚመሩ፣ ተወዳዳሪ፣ዘላቂ፣ ምርታማ ፣ ለሥራ እና ለኑሮ ምቹ ከተሞችን በ2030 ዓ.ም እውን ሆኖ ማየት ነው።"*

## ተልዕኮ

**በከተሞች መልካም አስተዳደርን በማስፈን ተደራሽ፣ ጥራት ያለው፣ ቀልጣፋ አገልግሎቶችን በማቅረብና መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት፣ ከተሞቹ እንደየሚናቸውና የመልማት አቅማቸው ከአካባቢያቸው ጋር ተሳስረው እንዲያድጉ በሚያስችል የተቀናጀ ፕላን እንዲመሩ ማድረግ ነው።**

# የፖሊሲው......

**መርሆዎች**

***ሀ)*** *አሳታፊ የከተማ ፕላን፣ ልማት እና አስተዳደር፣*

***ለ)*** *እኩልነት ፣ተደራሽነትና፣ ተጠቃሚነት፣*

***ሐ)*** *ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ግልፅ የሀብት አጠቃቀም እና አገልግሎት፣*

***መ)*** *ዘላቂ ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ልማት፣*

***ሠ)*** *የሕግ የበላይነትና ተጠያቂነት፣*

***ረ)*** *የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ፣*

***ሰ)*** *አካታች የከተማ ልማት፣*


***ሸ)*** *የባለድርሻ አካላት ትብብርና ጠንካራ ግንኙነት*

# 4.1 አጠቃላይ የፖሊሲው ግብና ዋና ዋና ዓላማዎች

## የፖሊሲው ግብ

- ዘላቂ፣ በፕላን የተቀናጀ፣ የተሳሰረ እና የተመጣጠነ የከተሞች ዕድገት ማምጣትና ለዜጎች የመኖሪያ ቤት ፣መሠረተ ልማት እና አገልግሎት፣ ቀልጣፋ ተቋማት በመፍጠር ከተሞች ለኑሮና ለሥራ ምቹ በማድረግ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገት መደገፍ ነው፡፡

**Goal**



# የዋና ዋና ዓላማዎች

I. የተቀናጀና ዘላቂ ፕላንና የአከታተም ስርዓት በመዘርጋት መተግበር፣

II. የከተማ አመራርና አስተዳደር ውጤታማ ማድረግ፣

III. የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻልና የአሠራር ሥርዓት ማጎልበት፣

IV. በከተሞች ውስጥ ቀልጣፋ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቶችን መገንባት፣

V. የከተማ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሠረተ ልማት ሥራዎችን ማስፋፋት፣

VI. በከተማና በገጠር የልማት ማዕከላት የቤት ልማት ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣

VII. ዘመናዊ የከተማ መሬት አስተዳደር እና የሪል ፕሮፐርቲ ግብይት መተግበር፣

VIII. በከተሞች የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት በማምጣት የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ማስቻል፣

IX. በአየር ንብረትና በሌሎች ተፈጥሮዊና ሰው ሠራሽ ክስተቶች የሚፈጠሩ ተጋላጭነት መቋቋም፣

X. የከተሞች ፅዳትና የአረንጓዴ ልማት አገልግሎት ማስፋፋት፣

XI. የከተሞች ሴፍቲኔትና ምግብ ዋስትና በማስፋፋትና በማሳደግ ድህነትን መቀነስ፣

# 5. የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮች፣ግቦችና አቅጣጫዎች

## 5.1 የከተማ ፕላንና አከታተም ሥርዓት፡

**የፖሊሲ ግብ**

- ከተሞች እርስበርስ ተደጋግፈውና ተሳስረው በፕላን እየተመሩ እንዲያድጉና የከተማ ፕላንና አከታተም ስራዎችን በተዋረዳዊ ሥርዓት መምራትና ማስፈጸም የሚችል አቅም እንዲገነባ ይደረጋል።

**አቅጣጫ**

- ከተሞች ዘላቂ ልማትን በሚያፋጥን በተቀናጀና ተዋረዱን በጠበቀ ፕላን እንዲመሩ ይደረጋል።
- የፕላን ዝግጅትና ትግበራ አቅም ይፈጠራል።
- የከተማ ፕላኖች ለመሬት አጠቃቀም ጥልቀት፣ ለሞቢሊቲና ለዘላቂ ልማት ልዩ ትኩረት ያላቸው ይሆናሉ።
- ግልጽና መሰረታዊ የከተማ ባህሪዎች የሚወከል የከተማ ትርጉም ይሰጣል።
- የከተማ-ከተማና የከተማ-ገጠር የልማት ተመጋጋቢነት ትስስር የተጠናከረ ይሆናል።
- ሁሉም አካባቢ በጸጋው/እምቅ አቅም/ መጠን የሚለማበት የተመጣጠነ ክትመት ይረጋገጣል።
- የከተሞች ፕላንና ልማት ከትልልቅ ፕሮጀክቶችና መሰረተ ልማቶች ጋር የተቀናጀና የሚናበብ ይሆናል፡

# 5. 2 የከተማ አስተዳደር፣ፋይናንስ እና አገልግሎት አሰጣጥ

## የፖሊሲ ግብ

➢ ውጤታማ የከተማ አመራር በመፍጠር ፣ መልካም አስተዳደር በማስፈን፣ዘመናዊ የፋይናንስና የሀብት አስተዳደር በመፍጠር፣ ቀልጣፋ፣ተደራሽና የዘመነ አገልግሎት በመስጠት የዜጎች እርካታ ደረጃ ከፍ እንዲል ይደረጋል፡፡

## አቅጣጫ

- ያልተማከለ አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
- የከተሞች መንግስታዊ እና የኮርፖሬት ሚና የሚመጥን መዋቅርና አሰራር ይዘረጋል፡፡
- የአገልግሎት ስታንዳርዶችን ማሻሻልና ማስተግበሪያ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡-
- ከተሞች አብዛኛውን የልማት ወጪዎቻቸውን በራሳቸው ፋይናንስ እንዲሸፍኑ ይደረጋል፡
- ከተሞች ለልማት ለመበደር የሚችሉበት የአሠራር ሥርአት ይዘረጋል፡-
- ከተሞች ጠንካራና ባህሪያቸውን ያገናዘበ የፋይናንስ እና የሀብት አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡

# 5.3 የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር

**የፖሊሲ ግብ**

ሕጋዊ፣ ፍትሐዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ የመሬት ዝግጅትና አቅርቦት ስራና ዘመናዊ የመሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ በማድረግ ለከተሞች ልማት፣ እድገትና ለዜጎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡

**አቅጣጫ**

- የመሬትን ሀብት ቆጥሮና ለይቶ ማወቅ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና የከተሞች የመሬት አጠቃቀም በጥናት ላይ የተመሰረተ ማድረግ ፡፡
- የከተሞች የመሬት ልማት አቅርቦትና ግብይት ተገማችና የተረጋጋ ማድረግ፡፡
- የከተማ መልሶ ማልማት አመራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡
- የከተማ ማስፋፋት አመራር ግልጽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
- የመሬት አስተዳደር ሥርዓት ለከተሞች ልማት የገቢ መሰረትና መጋቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
- የካዳስተር አተገባበር ሽፋኑ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

# 5.4 የቤቶች ልማትና አስተዳደር እና የሪል ፕሮፐርቲ ስርዓት

**የፖሊሲ ግብ**

- በከተማና በገጠር የልማት ማዕከላት የቤት ልማት እንዲስፋፋና አስተዳደሩ እንዲዘምን ማድረግና የሪል ፕሮፐርቲ ግመታ አሰራር በማሻሻል ገበያው የተረጋጋና ግልጽነት የሰፈነበት እንዲሆን ማድረግ ይሆናል፡፡

**አቅጣጫ**

- ለቤት መሥሪያ በቂ መሬት እንዲቀርብ ይደረጋል፡-
- አማራጭና ተደራሽ የቤት የፋይናንስ ስርዓት ይገነባል፡-
- የቤት ገበያው ግልጽ የተረጋጋ እንዲሆን ይደረጋል፡-
- የግል ዘርፍ ተሳትፎ እንዲጎለብትና የተለያዩ አማራጭ አቅሞች በሙሉ ሀይላቸው በቤት አቅራቢነት የሚሳተፉበት ሁኔታ ይመቻቻል፡-
- ዘመናዊ የግንባታ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ቤቶችን በፍጥነትና በጥራት ለመስራት  የሚያስችል ስርአት ይገነባል፡-
- የኪራይ ቤት አቅርቦት አማራጭ እንዲሰፋ ይበረታታል
- በገጠር ልማት ማዕከላት የሚካሄድ የቤት ግንባታ ስታንዳርድ ወጥቶለት የሚመራ ይሆናል፡፡
- ከተሞች የቦታ ደረጃ እንዲወጣላቸው ይደረጋል፡፡
- የሪል ፕሮፐርቲ ግመታ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡
- የሪል ፕሮፐርቲ ግብይት መረጃ ማሰራጫ የከተማ ማዕከላት ይገነባል፡፡

# 5.5 የከተማ መሠረተልማት

**የፖሊሲ ግብ**

የመሠረተ ልማት ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጎለብት በማድረግ፣የከተማ መሠረተ ልማት የነዋሪውን ፍላጎት መሠረት ባደረገና ፍትሐዊ ሥርጭትን በጠበቀ መልኩ እንዲቀርብ በማድረግ ሽፋኑ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

**አቅጣጫ**

- ለከተሞች የሚቀርበው መሠረተ ልማት የከተሞችን ሚና የሚመጥን እንዲሆን ይደረጋል፡-
- የከተማ መሠረት ልማት በቅንጅት እንዲመራ ይደረጋል፡፡
- የከተማ መሰረተ ልማቶች ስታንዳርዶች እንዲዘጋጁ በማድረግ፣ በከተሞች ተግባራዊ እንዲደረጉ ይደርጋል፡፡

# 5. 6. ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ

**የፖሊሲ ግብ**

የከተሞችን የጽዳት፣ የአረንጓዴ ልማትና ዉበት አገልግሎቶች ማስፋፋትና ለአየር ንብረት ለውጥና ለአደጋ ተጋላጭነታቸው ሊከላከልና ሊቋቋም የሚችል አቅም መፍጠር ይሆናል፡፡

**አቅጣጫ**

- የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ሥርአት በፕላን ተደግፎ የሚተገበር ይሆናል፡-
- የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና ማጓጓዝ ስራ ለነዋሪው ተደራሽና ምቹ እንዲሆን ይደረጋል፡-
- የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ፣ ማጓጓዝ እና አወጋገድ ወጥ ሥርዓት ይዘረጋል፡-
- ቆሻሻን የማከምና በአግባቡ የማስወገድ ሥርዓት ይዘረጋል፡-
- ዘላቂ ማረፍያ ቦታ አመዳደብና አመራር ሥርአት ይዘረጋል፤
- የከተሞችን ለአደጋ ተጋላጭነት ለሚቀንስ የሚያስችል ጥናትና ፕላንና ትግበራ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡
- የከተማ ልማታቻን የአካባቢ ደህነነትና ዘላቂ ልማትን ያረጋገጠ ይሆናል፡-

# 5.7 የከተማ ኢኮኖሚ ልማት

**የፖሊሲ ግብ**

በከተሞች የዳበረ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ምቹ መደላድሎችን መፍጠርና ድህነትን በመቀነስ ለከተማ ምግብ ዋስትና ችግሮች ፈጣንና ተገቢ ምላሽ መስጠት ይሆናል።

**አቅጣጫ**

- የከተማና የኢንዱትሪ ልማት እንደ አንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ተጣምረው ይመራሉ።ለኢንዱስትሪ ልማት ስኬት በቂ ቅደመ ዝግጅትና ቅንጅት በማድረግ የሚፈጸም ይሆናል።
- የተቀናጀ የከተማ ቅርስና ቱሪዝም መስህብ የመለየት፤ የመጠበቅና ማልማት ሥርዓት ይዘረጋል።የከተማ ግንባታችን ቅርስና ባህላችን የሚያጎላና የሚያንጸባርቅ ይሆናል።
- የከተማ ግብርና በከተማ መሬት አጠቃቀም ተገቢ ቦታ በመስጠትና እና ለከተማ ግብርና በቂና ተስማሚ የመሬት አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል፤
- የከተሞች ምግብ ዋስትናን በከተሞች ተደራሽ ለማድረግና በከተማ የሚገኘውን ድህነት ለመቀነስ  ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት ይዘረጋል፡-

# 5.8 አካታች የከተማ ልማት ሥርዓትና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግና ማጠናከር

## የፖሊሲ ግብ

በከተሞች ልማትና አገልግሎት አሠጣጥ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይ የሴቶችና፣የወጣቶችና፣የአረጋዊ ያን፣ሕፃናትና የአካል ጉዳተኞች ልዩ ፍላጎት ማካተትና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግና ማጠናከር ይሆናል፡፡


## አቅጣጫ

- የከተማ ልማት የሴቶችን እኩል ተሳታፊነትና ባለቤትነት እያረጋገጠ ይፈጸማል፡-
- የከተማ ልማት ወጣቱን በስፋት የሚጠቀምና ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል፡-
- የከተማ ልማታችን የህጻናትና አረጋዊያን ልዩ ሁኔታና ፍላጎት ያካተተ ይሆናል፡-
- የከተሞች ፕላንና ልማት የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ፣ ተደራሽነትና ተስማሚነት በማረጋገጥ የሚሠራ ይሆናል፡፡
- በከተማ ልማት የግል ባለሀብቱ ተሳትፎ እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡

# 6. ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስልት

- ለቀጣይ በየፖሊሲ ጉዳዮች፣ ግቦችና አቅጣጫዎች የማስፈጸሚያ ስልት ከፌደራል እስከ አከባቢ አስተዳደር ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው
- የተለዩ የፖሊሲ ጉዳዮች የህግ ማዕቀፎች ስላሉት መስተግበሪያ ስተራቴጂ ሆነው ይቀጥላሉ
- **ለፖሊሲው ትግበራ የሚያስፈልገው የፋይናንስና ሌሎች የድጋፍ ሥርዓቶች ይዘጋጃሉ።**

## 6.2 ፖሊሲው ቁልፍ አመላካቾች



አመሰግናለሁ!